# በውኑ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ አልሞተምን?

ከተስፋዬ ሮበሌ

ይህ ወንድም ተስፋዬ ሮበሌ፣ *"በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ! የአስተምህሮተ ትንሣኤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ ትንታኔ"* በሚል ርእስ ካዘጋጀው መጽሐፍ፣ ከምዕራፍ ሦስት በቀጥታ የተወሰደ ነው፡፡ በሙታን ትንሣኤ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ይህን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናበረታታለን፡፡

*"እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት፣ የሰው ልጆችን ኀጢአት ይቅር በማለት፣ ከእርሱ ጋር እንድንወዳጅ እንዲሁም የዘላለም ሕይወት ወራሾች እንድንሆን አድርጎናል" የሚለው የክርስትና መሠረተ እምነት ቢሆንም፣ የእስልምና ሃይማኖት ከዚህ ክርስቲያናዊ ትምህርት ጋር በተቃረነ መልኩ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም የሚል አቋም አለው፡፡ እንዲያውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ ሙስሊም መምህራን ኢየሱስ አልሞተም የሚለውን ትምህርት በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ዘዴዎች በመጠቀም በማሠራጨት ላይ ይገኛሉ፡፡ የዚህ ጽሑፍ ቀዳማይ ዐላማ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ቢሆንም፣ ከሞት ተነሥቶአል የሚለው የሙግት ነጥብ ሚዛን የሚደፋው ሞቱ በአጥጋቢ ማስረጃዎች ሲረጋገጥ ነው፡፡ "በዚህ ክፍል በርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶአልን?" የሚለውን ጉዳይ በጥሞና ለመመርመር የምንሞክር ሲሆን፣ ሙግታችን በአብዛኛው የሚያጠነጥነው፣ የእስልምና ሃይማኖት ምህራን አቋማቸውን ቆም እንዲያስቡ ሊያደርጓቸው ይችላሉ ያልናቸውን ታሪካዊ ማስረጃዎችን ነው[1]፡፡*

*የጥንት ሮማውያን ዝቅተኛ ናቸው የሚሏቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎችን፣ ባሮችን፣ ወታደሮችን፣ ዐመፀኞችንና ከሃዲዎችን በመስቀል ላይ በመቸንከር የመግደል ልማድ ነበራቸው[2]፡፡ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የኖረው ሃይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን* (Josephus)*፣ ኢየሩሳሌም በ*70 *ዓ.ም ስትፈርስ፣ ሮማውያን ወታደሮች አይሁዶችን አምርረው ከመጥላታቸው የተነሣ በርካታ ሰዎችን በተለየየ መልክ በመስቀል ላይ ቸንክረው*

---

[1] *የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በመቃወም ከበርካታ ክርስቲያን ፈላስፎችና የነገረ መለኮት ምሁራን ጋር በርካታ ክርክሮችን የሚያደርገው የሙስሊም ሃይማኖት ዐቃቤ እምነት እንዲሁም በቶሮንቶ ካናዳ የሚገኘው የእስልምና መረጃና የዳዋ ማዕከል ዓለም ዐቀፍ ማዕከል* (Islamic Information & Dawah Centre International in Toronto) *ፕሬዝዴንትና ኢማም የሆነው ሻቢር ዓሊ* (Shabir Ally)*፣ የፍልስፍናና የነገረ መለኮት ምሁሩ ፕሮፌሰር ዊልያም ሌን ክሬግ ጋር እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር የካቲት* 10 *ቀን* 2009 *ዓ.ም ባካሄደው ክርክር፣ የቁርኣንን* (*ቁርአን* 4÷157-158) *እንዲሁም የበርካታ ሙስሊም መምህራንን አስተምህሮ በሚቃረን መልኩ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶአል" ማለቱ ብዙዎችን አስደንቆአል፡፡ ሻቢር ዓሊ ወደዚህ ድምዳሜ መድረሱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በጠላቶቹ በሥቃየቱንና መዋረዱን ታሳቢ ያደረገ አነጋገር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ሙስሊሞች አላህ አገልጋዮን ለሥቃይና ለውርደት አሳልፎ አይሰጠውም ከሚለው አቋማቸው ጋር የሚጻረር ነው፡፡ በዚህ በሻቢር ዓሊ አዲስ አቋም ላይ አስተያየት የሰጡ ሰዎች፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶአል" ለሚለው ጉዳይ የሚቀርበው ታሪካዊ ማስረጃ እጅግ በርካታና በማያወላዳ መልኩ አሳማኝ ስለሆነ፣ የወሰደው የአቋም ለውጥ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡*

[2] *የክርስቶስን የመስቀል ሞት በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የሚከተሉትን መጻሕፍት ይመለከቷል* Martin Hengel, *Crucifixion* (Philadelphia: Fortress, 1977). Gerard S. Sloyan, *The Crucifixion of Jesus: History, Myth, Faith* (Minneapolis: Fortress, 1995), 18-22.

እንደ ገደሉ ዘግቧል[3]፡፡ ሮማዊው የታሪክ ጸሓፊ ሲሰሮ ሰዎችን በመስቀል ላይ ቸንክሮ መግደል የሮማውያን አሠቃቂና አስነዋሪ የወንጀለኛ መቅጫ ዘዴ ነው ሲል ጽፎአል[4]፡፡ ድርጊቱ እጅግ አሠቃቂ ከመሆኑም የተነሣ፣ "ይህ ዐይነቱ ድርጊት የሮማ ዜግነት ባላቸው ሰዎች ላይ እውን እንዳይሆን መደረግ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎችም በዚህ ዐይነቱ አሠቃቂ ቅጣት ሲቀጡ በዐይናቸው ማየት፣ በጆሮአቸው መስማት፣ በአእምሮአቸውም ማሰብ አይገባቸውም"[5] ሲል አስተያየቱን ሰጥቶአል፡፡ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሮማዊው የታሪክ ጸሓፊ ታኪተስ ሰዎችን በመስቀል ላይ ቸንክሮ መግደል፣ "ከገደብ ያለፈ ቅጣት"[6] ሲል ሐዘኔታውን ገልጾ ጽፎአል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ መገደሉን አራቱም ወንጌላት በስፋት የተረኩት ጉዳይ የመሆኑን ያህል፣ ክርስቲያን ያልሆኑ እንዲያውም የክርስትና ተቃዋሚ የነበሩ የታሪክ ጸሓፍያን ጭምር ክሥተቱን ሰፊ ቦታ ሰጥተው ተንትነውታል፡፡ አይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን፣ "ጲላጦስ ከእኛ ወገን በሆኑ ታላላቅ ሰዎች [ኢየሱስ] መወንጀሉን ሲሰማ፣ እንዲሰቀል ፈረደበት… "[7] ሲል ጽፎአል፡፡ በ115 ዓ.ም አካባቢ ታኪተስ፣ "ኔሮ ሮማ የመቃጠሏን ጉዳይ በጽኑ ያያያዘው ሕዝቡ ክርስቲያን ብሎ በሚጠራቸው ሰዎች ላይ ነው፤ ክርስቲያን የሚለው ስም መገኛ የሆነው ክርስቶስ የሚባለው ሰው በጠባርዮስ ቄሣር ዘመነ ንግሥና ጴንጤናዊው ጲላጦስ በተሰየመበት ዘመን ነው"[8]፡፡ የግሪካዊው ጸሓፊ የሳሞሳታው ሉቅያኖስ[9] በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መኻል ላይ፣ "እስከ ዛሬ ድረስ [ክርስቶስ የተባለውን] ሰው የሚያመልኩት ክርስቲያኖች፣ እጅግ የሚያከብሩትና ታሪካቸውን የቀረጸው [ኢየሱስ የተባለው] ሰው የተሰቀለው በዚህ ሕግ ነበር"[10]፡፡ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ማራ ባር ሴራፒዮን[11] የተባለ ሰው ከእስር ቤት ሆኖ ለልጁ በጻፈው ደብዳቤ ላይ የሚከተለው ሐሳብ ተከትቦበት ተገኝቶአል፣ "አይሁድ ጠቢቡን ንጉሣቸውን በመግደላቸው ምን ተጠቀሙ፤ ይህን ባደረጉም ቅጽበት ነው ንግሥናቸው ከእጃቸው አፈትልኮ የወጣው"[12]፡፡ ምንም እንኳ ማራ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መገደሉን ባይጠቅስም፣ መገደሉን ግን ጽፎአል፡፡ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ እንደ ተጻፈ የሚገመተው የዕብራውያኑ የትውፊት መጽሐፍ

---

[3] Gerard S. Sloyan, *The Crucifixion of Jesus:* ከJosephus, *Jewish Wars,* 5.451; Paul L. Maier, *Josephus: The Essential Works* (Grand Rapids: Kregel, 1994), 358. **ጠቅሶ ከጻፈው የተወሰደ፡፡**

[4] Sloyan, *Crucifixion of Jesus,* 13, ከ M. Tullius Cicero in Against Verress 2.5.64. In 2.5.165. **ጠቅሶ እንደ ጻፈው፡፡**

[5] Gary R. Habermas and Michael R. Licona, *The Case for the Resurrection of Jesu,* 49 ከCicero, *Pro Rabirio* 9-17 **ጠቅሰው እንደ ጻፉት፡፡**

[6] **ዝኒ ከማሁ፤** ከCornelius Tacitus, *The Annals* 15.44 **ጠቅሰው እንደ ጻፉት፡፡**

[7] **ዝኒ ከማሁ፤** ከJosephus, *Antiquities* 18.64. Josephus in Ten Volumes, Vol. 9, Jewish Antiquities, Loeb Classical Library, Louis, Louis H. Feldman, trans. (Cambridge, Mass.: Harvard University Press, 1981). **ጠቅሰው እንደ ጻፉት፡፡**

[8] **ዝኒ ከማሁ፤** ከTacitus, *Annals* 15.44 (C. A. D. 115) **ጠቅሰው እንደ ጻፉት፡፡**
**ጠባርዮስ ቄሣር የሮማው ቄሣር/ዐፄ ሲሆን፣ ክርስቶስ በተሰቀለበት ዘመን በሮማው ቄሣር ጠባርዮስ ተወክሎ ይሁዳን ያስተዳድር የነበረው ደግሞ ጴንጤናዊው ጲላጦስ ነው፡፡**

[9] "Lucian of Samosata"

[10] **ዝኒ ከማሁ፤** ከLucian of Samosata, *The Dath of Peregrine, 11-13* (C. mid-second century) **ጠቅሰው እንደ ጻፉት፡፡**

[11] Mara Bar-Serapion

[12] **በአሁኑ ጊዜ ይህ ታሪካዊ ሰነድ በብሪቲሽ ሙዝየም ውስጥ ይገኛል፡፡ ዝኒ ከማሁ** A. Roberts, J. Donaldson, and A. C. Coxe, eds. And trans., *The Ante-Nicene Fathers: Translations of the Writings of the Fathers Down to A.D. 325* (Oak Harbor, Ore.: Logos Research Systems, 1997). **ጠቅሰው ከጻፉት የተወሰደ፡፡**

ታልሙድ፣ "የፋሲካ በዓል በሚከበርበት ማግሥት እያሱ ተሰቀለ"[13] ይላል፡፡ የሹ ወይም እያሱ የሚለው ቃል ኢየሱስ ለሚለው የግሪክ ቃል አቻ ስያሜ ነው፡፡ ከእነዚህ ቀደምት ታሪካዊ ምንጮች በግልጽ የምንረዳው እውነት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መገደሉን ነው፡፡ ለዚህም ነው የክርስትናን መሠረተ እምነት በማሔሳቸው በስፋት የሚታወቁት ጆን ዶሚኒክ ክሮሳን፣ "የክርስቶስን ሞት በተመለከተ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መገደሉ ታሪክ ሊያረጋግጠው ይችላል ከሚባሉ ነገሮች ሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ሐቅ ነው"[14] ሲሉ የመሰከሩት፡፡

እጅግ በርካታና ጥንታዊ የሆኑ የታሪክ ሰነዶች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደ ተገደለ በግልጽ በሚያስተምሩበት ሁኔታ ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልተገደለም የሚል አቋም አላቸው፤ መገደሉ እውን ካልሆነ፣ ከሞት ተነሥቶአል የሚለው ጉዳይ እውነት ሊሆን በፍጹም አይችልም፡፡ እስልምና ከክርስትና እምነት ከስድስት መቶ ዓመት በኋላ የተቈረቈረ ሃይማኖት እንደ ሆነ በግልጽ ይታወቃል፡፡ እንዲሁም ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት አልተነሣም ለሚለው አቋማቸው በማስረጃነት አብዝተው የሚጠቅሷቸው ሁለት ሰነዶች ቁርአንና የባርናባስ ወንጌል በመባል የሚታወቁትን ጽሑፎች ነው (ቁርአን 4÷157-158፤ የባርናባስ ወንጌል 217)፡፡

የባርናባስ ወንጌል በመባል የሚጠራውን ሰነድ በተመለከተ፣ እጅግ በርካታ ሊቃውንት ይህ ሰነድ በዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በሙስሊሞች የተዘጋጀ ሐሳዊ ጽሑፍ እንደ ሆነ ይገልጻሉ[15]፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከላይ በናሙናነት የተመለከትናቸው እጅግ ጥንታዊ የሚባሉ የታሪክ ሰነዶች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደ ተገደለ ማስረዳታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ አልሞተም የሚል አንዳችም ጥንታዊ ሰነድ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሙስሊሞች የባርናባስ ወንጌል ሲሉ የሚጠሩት ሰነድ እርስ በርስ የሚቃረኑ እጅግ በርካታ ሐሳቦች ያሉበት መጽሐፍ እንደ ሆነ ምሁራን ያስረዳሉ[16]፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ

---

[13] ዝኒ ከማሁ፤ ከ*The Babylonian Talmud,* I. Epstein, ed. and trans. (London: Soncino, 1935-1952). ጠቅሰው እንደ ጻፉት፡፡ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የታጻፉ የአይሁድ ጽሑፎች ኢየሱስ ክርስቶስ ተኣምራትን ያደርግ እንደ ነበር እንዲሁም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደ ተገደለ በግልጽ ያስተምራሉ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል— John P. Meier, *A Marginal Jew: Rethinking the Historical Jesus,* 3 vols. (New York: Doubleday, 1991-2001), 1:96-97.

[14] ዝኒ ከማሁ፤ ከJohn Dominic Crossan, *Jesus: A Revolutinary Biography* (San Francisco: HarperCollins, 1991), 145:154:196:201 ጠቅሰው እንደ ጻፉት፡፡

[15] በመካከለኛው ዘመን የተጻፈ "የበርናባስ ወንጌል" በመባል የሚጠራ ሌላ ሐሳዊ ሰነድ ያለ ቢሆንም ይህ ሰነድ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ አልተሰቀለም የሚል ሐሳብ የለውም፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለም" የሚል ሐሳብ ያለው የባርናባስ ወንጌል በዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈው ጽሑፍ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል Norman L. Geisler and Abdul Saleeb, *Answering Islam* (Grand Rapids: Baker, 1995), 296.

[16] ይህ መጽሐፍ ከዐሥራ አምስተኛው እስከ ዐሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ተጻፈ የሚገመተው "የባርናባስ ወንጌል" በቅርቡ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጒሞ ለንባብ ቀርቦአል፡፡ የትርጒሙን ሥራ ያከናወኑትና ጸሑፉን ያስተረጐሙ ሰዎች ዋነኛ ዐላማቸው፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም የሚለውን አቋማቸውን ይህ ጽሑፍ እንዲደግፍላቸው በማሰብ ነው፡፡ ይህን ሐሰተኛ ጽሑፍ "የባርናባስ ወንጌል" ማለት ያስፈለገበት ቀዳማይ ምክንያት፣ የመጀመሪያ ክርስቲያኖች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ የሚለውን ጉዳይ አያምኑም ነበር ለማለት ተስቦ ነው፡፡ ባርናባስ ከጳውሎስና ከተቀሩት ሐዋርያት ጋር ወንጌልን የሰበከ እንዲሁም የአንጻኪያ ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረ ሰው መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ዛሬ ማንኛውም ሰው የፈለገውን መረጃ በኢንተርኔት ማግኘት በሚችልበት ጊዜ ይህ ዐይነቱን ስሕተት መፈጸም የሚያስተዛዝብ ነው፡፡ "እስከምታውቁ ድረስ ላሳስታችሁ" የሚለው ይህ ዐይነቱ አካሄድ፣ የግለሰቦቹን ምናልባትም እንቆምለታለን ያሉትን ሃይማኖት ተኣማኒነት በእጅጉ የሚሸረሽር ነገር ነው፡፡ አንባብያን ዛሬ ሙስሊሞች የባርናባስ ወንጌል ነው ስለሚሉት "ወንጌል" ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ

ቢያንስ በሁለት ቦታዎች ላይ ኢየሱስን “መሲሕ” የሚለው ሲሆን፣ በመጽሐፉ ቀጣይ ምዕራፎች ውስጥ ደግሞ ኢየሱስ “መሲሕ” ነው የሚለውን ሐሳብ በጽኑ ይቃወማል (ምዕራፍ 6 ከሚከተሉት ምዕራፎች ጋር ያነጻጽሯል 42: 70: 82: 96: 97: 198: 206)[17]:: ይህ ቅራኔ ግሪክ “ክርስቶስ” የሚለው ቃል በዕብራይስጥና በአረማይስጥ “መሲሕ” ወይም “የተቀማ” ማለት እንደ ሆነ በማያውቅ ሰው የተጻፈ ጽሑፍ እንደ ሆነ በግልጽ የሚያሳይ ነው:: አስደናቂ የሆነው ሌላው ጉዳይ፣ ይህ የባርናባስ ወንጌል በመባል የሚጠራው ሰነድ የኢዮቤልዩ ዓመት በመቶ ዓመት አንዴ እንደሚከበር የሚያስተምር ቢሆንም (የባርናባስ ወንጌል 83)፣ በዓሉ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በየመቶ ዓመቱ ይከበር የሚል አቋም በ1343 ዓ.ም ላይ ከማውጣቷ በፊት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በዓሉን የምታከብረው የባርናባስ ወንጌል እንደሚያስተምረው በየመቶ ዓመቱ ሳይሆን በየሃምሳ ዓመቱ ነበር[18]:: ከዚህም ይልቅ አስደናዊ የሆነው ጉዳይ የባርናባስ ወንጌል በመካከለኛው መቶ ዘመን ስለተነሣው የፊውዳሊዝም[19] ሥርዐተ ማኅበር (የባርናባስ ወንጌል 122)፣ በመካከለኛው ዘመን ላይ ስለነበረው የፍርድ ሥርዐት (የባርናባስ ወንጌል 121)፣ እንዲሁም በእንጨት ስለመሥራ የወይን መጭመቂያ ይገልጻል (የባርናባስ ወንጌል 152)፣ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ለወይን ማስቀመጫነት በአገልግሎት ላይ ይውል የነበረው የወይን አቀማመጥ ነበር::

ከእነዚህና ከእነዚህ ጋር ተዛማጅነት ካላቸው በርካታ ማስረጃዎች በግልጽ የምንማረው ሐቅ፣ የባርናባስ ወንጌል የሚባለው ጽሑፍ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶአል ወይስ አልሞተም የሚለውን ክርክር ለመዳኘት ብቃት የሌለው ክርስቶስ ከሞተ ከ1500 እስከ 1700 ዓመት በኋላ የተጻፈ ጽሑፍ ነው:: ስለዚህ ይህን ሰነድ እንደ ትልቅና ተኣማኒ የታሪክ ሰነድ በመቀበል የሃይማኖት አስተምህሮን ማዋቀር ስሕተት ነው::

ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶአል የሚለውን የወንጌል ትምህርት የማይቀበሉበትን ሌላው ምክንያት፣ ቁርአን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱን አያስተምህር እንዲያውም ተቃራኒውን መረጃ ይሰጣል ስለሚሉት ጉዳይ ደግሞ አስተያየታችንን እንስጥ:: በዚህ ረገድ ቁርአን ያለውን ትምህርት በጥሞና ለመመርመር፣ ቁርአን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን በጎ ፈቃድ በምድር ላይ እንዴት እንደሚያሰፍን ያስተምራል የሚለውን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር መመልከቱ ተገቢ ይሆናል::

እግዚአብሔር ለእኛ ሲል ከእኛ ጋር በመሆን መከራን ይቀበላልን? እግዚአብሔር በሰብአውያን ሕይወት ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ ያደርጋልን? እግዚአብሔር መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት የጦርን ኀይል ይጠቀማልን? እግዚአብሔር አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የእርሱ ተከታዮች ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ ያስተምራልን? የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ሰው ምድራዊ መከራ ያጋጥመዋልን? ሙስሊሞች ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ አዎንታዊ ሲሆን፣ ክርስቲያኖች ግን አሉታዊ በሆነው ምላሽ ይጸናሉ:: ይህ ጉዳይ ሙስሊሞችና

---

Norman L. Geisler and Abdul Saleeb, *Answering Islam* (Grand Rapids: Baker, 1995), 295-299 ይመለከቷል፤ እንዲሁም ተጨማሪ መረጃዎችን ከኢንተርኔት ላይ ማግኘት ከፈለጉ የሚከተሉትን ይመልከቱ:—

<http://www.chrislages.de/barnarom.htm>, <http://en.wikipedia.org/wiki/Gospel_of_Barnabas>, <http://answering-islam.org/Barnabas/index.html>, <http://answering-islam.org/Barnabas/saleeb.html>, <http://www.answeringislam.info/Barnabas/chap_I.html>.

[17] Gary R. Habermas and Michael R. Licona, *The Case for the Resurrection of Jesu,* 184.

[18] Geisler and Abdul Saleeb, *Answering Islam* appendix 3 ይመለከቷል::

[19] "ፊውድ" ማለት ሰፋፊ የመሬት ይዞታ ማለት ሲሆን፣ ፊውዳሊዝም ሰፋፊ መሬቶች የምርት ዋነኛ መሠረቶች የሆኑበትና በግል የተያዙበት ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሥርዐት ነው::

ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቀለ ለሚለው ትምህርት የሚሰጡትን ምላሽ ይወስነዋል፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ክርስትናም ሆነ እስልምና የሚሰጡትን ምላሽ በጥንቃቄ ከመረመርን፣ የልዩነቱን ምክንያት አጥርተን ስለምንረዳ የልዩነቱን ምክንያት አበጥሮ ለማየት ጥሩ መዳላድል ይሆንልናል፡፡

እንደ ወንጌላት ትምህርት ክርስቶስ ኢየሱስ ወደዚህች ምድር የመጣበት ቀዳሚይ ዐላማ ተኣምራትን ማድረግ ሳይሆን፣ የሰው ልጆች በኀጢአታቸው ምክንያት የመጣባቸውን ዘላለማዊ ኵነኔና ከእርሱም ጋር ተዛማጅ ከሆኑ ማናቸውም መዘዞች ዐርነት ማውጣት ነው፣ “የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ፣ ሊገለገል አልመጣምና” (ማርቆስ 10÷45)፡፡ “ነገር ግን ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል” (ሮሜ 5÷8)፡፡ እጅግ ታዋቂ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ ጕዳዩን በዚህ መልክ ይገልጸዋል፣ “'በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና” (ዮሐንስ 3÷16)፡፡

እንግዲያው፣ “ቅዱሳት መጻሕፍት እንሚሉት፣ ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ” (1ቆሮንቶስ 15÷3-4) የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እግዚአብሔር ለሰው ለጆች ያለውን ታላቅ ፍቅር አመልካች ነው ወይስ እንደ ሙስሊም መምህራን ትምህርት ያልተሰቀለውን ተሰቀለ፣ ያልሞተውንም ሞተ የሚል ስሑት አስተሳሰብ?

ቀድሞ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቄስ የነበሩ፣ አሁን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በመቃወም በሚጽፉአቸው መጻሕፍትና በሚያደርጓቸው ክርክሮች በስፋት የሚታወቁት ጆን ዶሚኒክ ክሮሳን፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ትእዛዝ፣ በበመስቀል ላይ መሞቱ ታሪክ በአንድ ድምፅ የሚያረጋግጠው ሐቅ ነው”[20] ሲሉ መስክረዋል፡፡ አራቱም ወንጌላት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደ ሞተ በግልጽና በስፋት ያስተምራሉ፡፡ ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ እጅግ በርካታ ታሪካዊና ተኣማኒ ሰነዶች ለምሳሌ ሮማዊው የታሪክ ጸሓፊ ታኪተስ፣ አይሁዳዊው የታሪክ ምሁር ዮሴፍ ወልድ ኮርዮን እንዲሁም የዕብራውያን የታሪክና የሃይማኖት ሰነድ ታልሙድ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ እንደ ሞተ በግልጽ ይናገራሉ[21]፡፡ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የተጻፈ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም የሚል አንዳችም የታሪክ ሰነድ የለም[22]፡፡

ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስ በጠላቶቹ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም ወደሚለው ድምዳሜ ካደረሳቸው ምክንያቶች መኻል፣ አምላክ መልእክተኛውን እንዴት አሣቃቂ ለሆነው ለመስቀል ሞት አሳልፎ ይሰጠዋል የሚለው ጕዳይ፣ ከሙግቱ መኻል መሠረታዊው ነጥብ ነው፡—

---

[20] John Dominic Crossan, *Who Killed Jesus? Exposing the Roots of Anti-Semitism in the Gospel Story of the Death of Jesus* (San Francisco: Harper, 1995), 5.

[21] ስለ ክርስቶስ ምድራዊ ሕይወትና ሞት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ ሰነዶች የሚሰጡትን እማኝነት በስፋት መመልከት ከፈለጉ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል፡— F. F. Bruce, *Jesus and Christian Origins Outside the New Testament* (Grand Rapids: Eerdmans, 1974).

[22] Hengel, *Crucifixion* (Chap. 13, n. 5).

> "እኛ የአላህን መልእክተኛ፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፤ ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ፤ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ መገደል በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም:: ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው" (ሱራ 4÷157-158 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

ይህን የቁራን ጥቅስ በተመለከተ የእስልምና ሃይማኖት ምሁሩ ዶክተር ዴቪድ ሼንክ እንዲህ ይላሉ፣ "ይህ የቁራን ዐውድ በነቢዩ መሐመድ የተነገረው፣ በመዲና የሚኖሩ አይሁዶች ከሙስሊሞች ጋር ግጭት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ነው:: መሐመድ ኢየሱስ መሲሕ ነው ነገር ግን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም ሲሉ አይሁዶችን ተቃወሙ"[23]::

ሙስሊሞች ኢየሱስ መስሕ እንደ ሆነ ያምናሉ፤ መሲሕ መሆኑ የሚረጋገጠውም ለሞት ተላልፎ በመሰጠቱ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ተኣምራዊ በሆነ መንገድ ከጠላቶቹ ነጻ ሲያወጣው ነው የሚል አቋም አላቸው:: ነገር ግን ይህ ጉዳይ ወንጌላትም ሆኑ መዝሙራት መሲሑ ለሞት ተላልፎ እንደሚሰጥ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር የሚጻረር ነው[24]:: ሙስሊሞች ኢየሱስ ጠላቶቹ ሳይሰቅሉት በቀጥታ ወደ ሰማይ ዐርጓል የሚል አቋም ያላቸው ሲሆን፣ በእርሱ ፈንታ ሮማውያን በስሕተት የሰቀሉት አስቆሮቱ ይሁዳ ነው የሚል ግምት አላቸው:: በቢልዮን የሚቈጠሩ ሙስሊሞችም ይህን ጉዳይ እውነት እንደ ሆነ ይቀበላሉ::

በርካታ ማስረጃዎች ይህ የሙስሊሞች አቋም በርካታ ችግሮች አሉበት:: ይኸውም **አንደኛ፤** ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም የሚል አንዳችም ታሪካዊ ሰነድ የለም[25]:: **ሁለተኛ፤** ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን የሚያስረዱ እጅግ በርካታ ታሪካዊ ሰነዶችን ለክርስቶስ ትንሣኤ ታሪካዊ ማስረጃ በሚለው ርእስ ሥር በስፋት ለማቅረብ እንሞክራለን:: ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ተነሥቶአል የሚለው ሐቅ ኢየሱስ መሞቱን ታሳቢ ያደረገ ነው:: **ሦስተኛ፤** የተለያዩ ምንጮች የኢየሱስ ክርስቶስ ባልንጀሮችና ቤተሰቦች እንዲሁም እናቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ መቀበሩን ዘግበዋል (ሉቃስ 23÷49-59፤ ዮሐንስ 19÷25-27:38-42)::

ሙስሊሞች እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ አስቆሮቱ ይሁዳን ወይም የተሰቀለውን ሰው በተክለ ሰውነቱም ሆነ በገጹ ኢየሱስን እንዲመስል አድርጎታል የሚል እምነት አላቸው:: አንዳንዶች ደግሞ የተሰቀለው ሰው፣ ሰው ሳይሆን ኢየሱስን የሚመስል ቁሳዊ ነገር ግን ነው የሚል አቋም አላቸው:: ይህ ትንታኔ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት:: ***አንደኛ፤*** ይህን ትንታኔ የሚያጸና አንዳችም ታሪካዊ ሰነድ የለም:: ***ሁለተኛ፤*** ይህ ትንተና አምላክን አጭበርባሪ/አሳሳች አድርጎ የሚያቀርብ ትንተና ነው:: እግዚአብሔር ኢየሱስ ያልሆነውን ሰው ኢየሱስ አስመስሎ ማቅረቡ እንዲሁም ከዚህ የተነሣ ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ተሰቅሎአል ብለው በስበካቸው ስሕተት ነው:: አምላክ ያሳሳተው ሰቃዮቹን ብቻ ሳይሆን፣ ደቀ መዛሙርቱንም ጭምር መሆኑን ልብ ይሏል::

---

[23] ዴቪድ ሼንክ፤ *የሺህ ዓመት ጉረቤታሞች ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2000 ዓ.ም), 171::

[24] *ቁራን የሙሴ መጻሕፍት፣ መዝሙርና ወንጌል ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረዱ የአምላክ ቃል ናቸው የሚል ትምህርት ያስተምራል::*

[25] Norman L. Geisler, *Baker Encyclopedia of Christian Apologetics,* Baker Reference Library (Grand Rapids: Baker, 1999), 67-69.

ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም የሚለው ትምህርታቸው የሚመነጨው ኢየሱስን እንደ ሌሎቹ ነቢያት ነቢይ አድርጎ ከሚመለከተው አስተሳሰባቸው እንዲሁም እግዚአብሔር አገልጋዩን በሞት በተለይ ደግሞ አሠቃቂ በሆነው የመስቀል ሞት እንዲሞት አይፈቅድም ከሞለው አቋማቸው ነው::

በርግጥ እግዚአብሔር ከሃሌ ኩሉ የሆነ አምላክ ነው:: ቁርአንም የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት በዚህ መልኩ ይገልጸዋል:—

> "አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ሕያው፣ ራሱን ቻይ ነው፤ ምንገላጀትም፣ እንቅልፍም አትይዘውም፤ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው፤ ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፤ በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)፤ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ፤ ጥበቃቸውም አያቅተውም፤ እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው" (ሱራ 2÷255 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

ቁርአን 99 ናቸው የሚላቸውም የእግዚአብሔር ስሞች መኻል አብዛኞቹ ስሞች የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት የሚያስተምሩ ናቸው:: "አል-አዚዝ" "በግርማው ልዑል የሆነ" (59÷23)፣ "አል-ዓሊ" "ልዑል" (2÷255-56)፣ "አል-ቃድር" "ከሃሌ/ችሎታ ያለው" (17÷99-101)፣ "አል-ቋዱስ" "በቅድስናው ከሁሉ በላይ የሆነ" (62÷1)፣ "አል-ሙታሊ" "በራሱ ከፍ ያለ" (13÷9-10)፣ "አል-ሙኢዝ" "ክቡር" (3÷26)፣ "ማሊክ አል-ሙላክ" "የመንግሥት ባለቤት የሆነ" (3÷26)፣ "አል-ዋህድ" "አንድያው" በመለኮታዊ ልዕልናው ልዩ የሆነ (13÷16-17)፣ "አል-ዋሂድ" "ልዩ የሆነ" (74÷11)፣ "አል-ዋኪል" "ገዢ" (6÷102)[26]:: በርግጥ እግዚአብሔር ያሻውን ነገር የሚያከናውን አምላክ ከሆነ፣ አገልጋዩ እንዲሞት የማይፈቅድበት ምክንያት ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት የሚረጋገጠው ክርስቶስ እንዳይሞት በመታደግ ብቻ ነውን? አገልጋዩ ቢሞት እንኳ የሞትን ጣር አጥፍቶ ከሞት ሊያስነሣው አይችልም የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? እንዲያውም አንዳንድ የቁርአን ምንባባት ኢየሱስ ክርስቶስ መሞቱንና ከሞት መነሣቱን እንደሚናገሩ አንዳንድ ምሁራን ያስረዳሉ[27]፤ ለምሳሌ የሚከተለውን የቁርአን ክፍል ይመለከቷል:—

> "በርሱ ያዘዝኸኝን ቃል ጌታየንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለእርሱ ሌላ አላልኩም፤ በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በእነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ፤ በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ) ጊዜ አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ፤ አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ" (ሱራ 5÷17 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

እግዚአብሔር ልዑል መሆኑን የምናምን ከሆነ ምን መሥራት እንዳለበትና ምን መሥራት እንደሌለበት እኛ ልናሳየው ወይም ልንወስንለት አይገባም:: ለዚህም ነው በነቢዩ ኢሳይያስ፣ እግዚአብሔር የሚከተለውን ንግግር የሚናገረው:—

> "ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ፣ መንገዴ እንደ መንገዳችሁ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር"
> (ኢሳይያስ 55÷8)

እንዲያውም ነቢዩ ኢሳይያስ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደሚሞት ከሰባት መቶ ዓመት በፊት እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሮ ነበር:—

---

[26] ዝኒ ከማሁ፤ 143::
[27] ዝኒ ከማሁ::

> “በፊቱ እንደ ቡቃያ፣ ከደረቅም መሬት እንደ ወጣ ሥር በቀለ፤ የሚስብ ውበት ወይም ግርማ የለውም፤ እንድንወደውም የሚያደርግ መልክ አልነበረውም። በሰዎች የተናቀና የተጠላ፣ የሕማም ሰውና ሥቃይ ያልተለየው ነበር። ሰዎች ፊታቸውን እንደሚያዞሩበት ዐይነት፣ የተናቀ ነበር፤ እኛም አላከበርነውም። በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፣ እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው። ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን” (ኢሳይያስ 53÷2-5)

ሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ይህንኑ እውነት ትንቢታዊ በሆነው ክፍላቸው ያረጋግጡልናል (የሚከተሉትን ክፍሎች በናሙናነት ይመለከቷል መዝሙር 22÷16፤ ዘካርያስ 12÷10)። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት የማያምኑትን ሰዎች እንደሚያሰናክል ያስተምራሉ፣ “ከእግዚአብሔር ጥበብ የተነሣ ዓለም በገዛ ጥበብዋ እግዚአብሔርን ማወቅ ስለ ተሳናት፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአል” (1ቆሮንቶስ 1÷21) “ምክንያቱም ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፤ ከሰውም ብርታት ይልቅ የእግዚአብሔር ድካም ይበረታል” (1ቆሮንቶስ 1÷25)።

እግዚአብሔር ኢየሱስን እንዳይሞት ሳይሆን ያደረገው ከሞተ በኋላ ከሞት ነው ያስነሣው፣ “እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አስወግዶ አስነሣው፤ ሞት ይዞ ሊያስቀረው አልቻለምና” (ሐዋርያት ሥራ 2÷24) “አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወለድሁህ” (ሐዋርያት ሥራ 13÷33)። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኪዳኑን የሚጠብቅ አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል (መዝሙር 16÷10)። ስለዚህም ይህን ኪዳን እውን ያደረገው ኢየሱስን ከሙታን በማስነሣት ነው፣ “ይህንን አስቀድሞ በማየቱ እርሱ በሲኦል እንደማይቀርና ሥጋውም እንደማይበሰብስ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ተናገረ” (ሐዋርያት ሥራ 2÷31) ስለዚህ ክርስቶስ፣ “በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ” አለ (ሐዋርያት ሥራ 2÷33)።

ከእስልምና ሃይማኖት መምህራን ጋር በተየያዘ መንገድ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ሞት ይህን ያህል ከተነጋገርን፣ “የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር” በመባል የሚታወቀው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት ኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀሉን ቢያምንም ሁሉም ክርስቲያናዊ ትውፊቶች ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር በተቃረነ መልኩ ኢየሱስ የተሰቀለው በመስቀል ላይ ሳይሆን ቀጥ ባለ እንጨት ወይም ምሰሶ ላይ ነው የሚል እምነት አለው። በመሠረቱ ክርስቶስ ለኀጢአታችን መሞቱ እንጂ አሟሟቱ በመስቀል ላይ ምን ይመስል ነበር የሚለው ጉዳይ ለክርስትና መሠረተ እምነት አንዳችም እርባና የለውም። የሃይማኖት ድርጅቱ በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን መሠረተ እምነት ማጣጣልና ራሱን ልዩ አድርጎ ለማቅረብ ካለው ፍላጎት የተነሣ በዚህም ጉዳይ ላይ በታሪክ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ ትንተና ለመስጠት ሙከራ ሲያደርግ ይታያል። በዚህ ጉዳይ ላይ የተወሰኑ አስተያየቶችን ሰጥቶ ማለፍ አግባብ ስለመሰለን ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡ ጽሑፎች በጉዳዩ ላይ የሚሰጡትን አስተያየት በአጭር እንመርምር።

በይሖዋ ምስክሮች ተዘጋጅቶ ከጥቂት ወራት በፊት ለንባብ የበቃው የክርስቲያን፣ “ግሪክኛ ቅዱሳን መጻሕፍት አዲስ ዓለም ትርጒም” ኢየሱስ ክርስቶስ፣ “ቀጥ ያለ እንጨት ወይም ምሰሶ ወይም ደግሞ ለመሠረት የሚያገለግል ዐምድ” ላይ እንጂ መስቀለኛ እንጨት እንዳልሆነ ይገልጻል (ገጽ 416-418)።

ድርጅቱ ወደዚህ ድምዳሜ ላይ አድርሰውኛል የሚላቸው ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡—

(1) "በጥንቱ የግሪክ ቋንቋ ስታውሮስ የሚለው ቃል ቀጥ ያለ እንጨት ወይም ምሰሶ ወይም ደግሞ ለመሠረት የሚያገለግል ዐምድ ማለት ነው...ስታውሮስ የሚለውን ቃል የተጠቀሙበት ልክ እንደ ጥንቱ ግሪክኛ የትኛውም ቦታ ላይ ምንም ዐይነት መስቀለኛ እንጨት ወይም ምሰሶ ለማመልከት ነው። ቃሉ መስቀልን እንደሚያመለክት የሚያሳይ ምንም ዐይነት ማስረጃ የለም። ሐዋርያው ጴጥሮስና ሐዋርያው ጳውሎስም ኢየሱስ የተቸነከረበትን የመከራ እንጨት ለማመልከት ዛይሎን የተባለውን ቃል ተጠቅመዋል፤ ይህ ደግሞ መስቀለኛ እንጨት የሌለውን ቀጥ ያለ እንጨት ያመለክታል፤ ዛይሎን በዚህ ለየት ያለ አገባቡ የሚያመለክተው ይህንን ነው"[28]።

(2) "የአረማውያንን የመስቀል ፅንሰ ሐሳብ በመንፈስ መሪነት ወደ ተጻፉት ቅዱሳን መጻሕፍት በማስገባት በጽሑፍ በሰፈረው የአምላክ ቃል ላይ ምንም ነገር መጨመር አንፈልግም"[29]።

"ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" በመባል የሚታወቀው የድርጅቱ የክርክር ማስተማሪያ መጽሐፍ፣ ከክርስትና በፊትም ሆነ ከክርስትና እምነት በኋላ እጅግ በርካታ አረማዊ እምነቶች መስቀልን እንደ ሃይማኖት ምልክታቸው አድርገው ይቀበሉ እንደ ነበር፣ ይኸው እምነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ በመግባት የክርስትናም ምልክት እንዲሆን ተጽእኖ እንደ ፈጠረ ያብራራል[30]።

ይሖዋ ምስክሮች በስቀልን ብቻ ሳይሆን ዋና ዋና የሚባሉትን የክርስትና መሠረተ እምነቶች ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ የተቀዱ መሆናቸውን ለማስረዳት ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸው የተለመደ አካሄዳቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ድርጅቱ በቀድሞዎቹ ዘመናት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንኳ አልሞተም የሚል አቋም ነበረው[31]። ክርስቶስ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በምትቀበለው ዐይነት መልኩ በተዘጋጀ እንጨት ላይ እንጂ ቀጥ ባለ አንድ እንጨት ላይ እንዳልተሰቀለ የሚያመለክቱትን ዋና ማስረጃዎች በቅኝት መልክ እንመልከት:— (1) ሮማውያን ሰዎችን ሰቅለው የሚገድሉበት መስቀል የሚከተሉትን ቅርጾች እንዳሉት ታሪክ በግልጽ ያስተምራል (T)፣ (X)፣ (†) በበርካታ የታሪክ ምሁራን የሚታመነው ኢየሱስ በክሩክስ ኢሚሳ ወይም የላቲን መስቀል ተብሎ በሚጠራው የመስቀል ቅርስ እንደ ሞተ ነው[32]። (2) የሃይማኖት ድርጅቱ መሥራች ቻርለስ ታዝ ራስል በጽሑፎቹ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተለመደው ዐይነት መልኩ እንደ ሞተ አስተምሮአል። እንዲሁም የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዴንት ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ የሥልጣን ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በጻፉቸው መጻሕፍት (ለምሳሌ "ተፈጥሮ" እንዲሁም "የእግዚአብሔር በገና")[33]፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በተለመደው መንገድ በመስቀል እንደ ሞተ ቢያስተምርም፣ በ1936 ዓ.ም ላይ ግን ሐሳቡን በመቀየር አሁን ድርጅቱ የሚያስተምረውን ትምህርት ማስተማር ጀምሮአል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ ማለት አረማዊ አምልኮ ከሆነ፣ ድርጅቱ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት አረማዊ አምልኮ ያካሄድ ነበር ማለት ነው[34]፣ (3) የጥንት ክርስቲያኖች መልእቅንና ዓሣን የሃይማኖታቸው ምልክት አድርገው ይጠቀሙ ነበር። ነገር ግን የሃይማኖት ፈቃድ አግኝተው ስደቱ ጋብ ሲል የጥንት ክርስቲያኖች መስቀልን እንደ ምልክት መጠቀም ጀመሩ። የሮማው ንጉሡ ነገሥት ቈስጠንጢኖስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጦልኝ መስቀል ዐርማ አድርገህ ብትወጣ

[28] የክርስቲያን ግሪክኛ ቅዱሳን መጻሕፍት አዲስ ዓለም ትርጉም ገጽ 417።

[29] ዝኒ ከማሁ።

[30] "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" 87-91

[31] "No Biblical evidence even intimates that Jesus died on a cross" (*Awake!*, 8 November 1972)

[32] (1). The crux simplex (I), a "single piece without transom". (2). The crux decussata (X), or St.Andrew's cross (3). The crux commissa (T), or St. Anthony's cross (4). The crux immissa (†), or Latin cross.

[33] "Creation", "Harp of God"

[34] "Creation", ገጽ 265 እና 336 ይመለከቷል።

*ድል ትነሣለህ አለኝ ብሎ እንደ ነበር ታሪክ ይገልጻል፡፡* (4) *በሥነ ቊፋሮ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ሮማውያን ሰዎችን ሰቅለው የሚገድሉበት መስቀል ቀጥ ያለ እንጨት እንዳልነበረ ያመለክታል*[35]*፡፡* (5) *ቀደምትና ደኃርት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ለምሳሌ ዮስጦስ ሰማዕት፣ ሔሬኔዎስ፣ ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ፣ ተርቱልያኖስ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ለሃይማኖቱ ትእምርት አድርጎ የሚጠቀምበትን ዐይነት መስቀል በጽሑፎቻቸው ጽፈው ተገኝተዋል፡፡* (6) *ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ቀጥ ባለ ዐምድ ላይ ሳይሆን በመስቀል እንደ ሞተ የሚያረጋግጥ ፍንጭ አላቸው፡፡ ለምሳሌ እጆቹ ከአንድ በላይ በሆኑ "ምስማሮች" እንደ ተቸነከሩ (ዮሐንስ* 20÷25)[36]*፣ "በራሱ ላይም፣ 'ይህ የአሁድ ንጉሥ ኢየሱስ ነው' የሚል የክሱን ጽሕፈት ጽፈው አኖሩ" (ማቴዎስ* 27÷37) *የሚለው ቃል "ይህ የአሁድ ንጉሥ ኢየሱስ ነው" የሚለው ጽሑፍ በእጆቹ ላይ ሳይሆን በራሱ ላይ መሆኑ፣ ኢየሱስ ይሖዋ ምስክሮች በሚሉት መልኩ እንዳልተሰቀለ የሚያስተምር ነው፡፡ በተጨማሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስ በምን ዐይነት ሞት እንደሚሞት በገለጸበት ቦታ "እጅህን ትዘረጋለህ" ዮሐንስ* 21÷18-19 *የሚለው ቃል አሚሚቱ በመስቀል ላይ እንደ ሆነ የሚያስተምር ብቻ ሳይሆን መስቀል እጅን ዘርግተው የሚሰቀሉበት አሚሚት እንደ ሆነ የሚያመላክት ነው፡፡* (7) *ክርስትና ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተ የሚለውን ጒዳይ ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አምላኪያን ለሃይማኖታቸው ትእምርት ያደርጉት የነበረ ምልክት ነው የሚለው አስተሳሰብ ስሑት ነው፡፡ አንደኛ፡— ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደ ሞተ ያስተምረናል፡፡ ሁለተኛ፡— የጥንቷ ቤተ የክርስቶስን መስቀል እንደ ምልክት ትጠቀምበት ነበር፤ ሦስተኛ፡— ቃሉ ሌጣ እንጨትን የሚያመለክት ቢሆንም ሮማውያን ወንጀለኞችን ቀጥ ባለ እንጨት ሳይሆን ቅርጹ በተለያየ መስቀል ላይ ወንጀለኞችን ይገድሉ ነበር፡፡ አራተኛ፡— አረማውያን መስቀልን እንደ ትእምርት አድርገው ተጠቅመዋል እንኳ ብንል፣ ክርስቲያኖች እንዳይጠቀሙበት የሚከለክላቸው ምክንያት የለም፡፡ ሰዎች በኢየሱስ ስም በዙ ክፉ ነገር አድርገዋል፣ በስሙ ክፉ ተፈጽሞ ያውቃል በሚል ስሙን መጥራት ወንጀል ሊሆን እንዴት ይችላል?*

---

[35] Michael Green, *Evangelism in the Early Church*, 214-215 *Biblical Archaeological Review*, January/February, 1988, pp. 48-49.

[36] *በቅርቡ ድርጅቱ ከአስተምህሮው ጋር እንዲጣጣም በሚል ያዘጋጀውም መጽሐፍ እንዲሁም የእንግሊዝኛው ኢንተር ሊንየር "ምስማሮች" ሲል ተርጒሞአል፡፡*